የዘረኝነት አንድ መንስዔ ቀደምት አበውን እንደ ግለሰቦች በመመልከት ፈንታ፥ የዝርያቸው ሁሉ ግንድ ወይም ተምሳሌት አድርጎ መውሰድ ነው። ሸክስፒር ግለሰብ ነበር። የእንግሊዛዊ ዜጋ ሁሉ ጭማቂ አይደለም። ቢወክልም ሰብአዊ ፍጡርን በመላ እንጅ የአካባቢውን ሰዎች ብቻ አይደለም። ታላቅነቱም በዚህ ኩለንተናዊነትን በማንጸባረቅ እንጅ በአገሩ መልክአ ምድር ብቻ ቢከፈፍ ኖሮ በተመጠነ ነበር። በዘር ጥራት ረገድ ብቻ ለምን ኩዋሂላዎች ተለይተው ይጠቀሳሉ? አንድ ሼክስፔር ቢኖር አንድ ሺ ደደብ እንግሊዝም ይኖራል። አህያ ኢትዮጵያም ውስጥ አህያ ናት፥ እንግሊዝም ሩሲያም ውስጥ። ዝግባም እንደዚሁ፥ ጽጌረዳም። እርግጥ የመንፈስ ኩራት ለማስገኘት ማንኛውም ጥራት ያለው ህያው ሆነ ግዑዝ ነገር መንስዔ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ኩራት ወደ ትዕቢትነት ተለውጦ የበላይነትን መንናጸፊያ ሊሆን አይገባውም። ራሱን እንደ ላዕላይ ፍጡር ለመቁጠርና ሌላውን እንደ ዝቅተኛ ፍጡር፥ እንደ ከብት የሚያስመለክት ከሆነ የጉድለት እንጅ የምልዓት መሳሪያ አይሆንም።

እንደዚሁ የዘር ስንጠቃ በነገስታት ደረጃም ውስጥ እንደሚገኝበሻ አሸብር የሰለሞንና የሳባን ታሪክ ሲመዙ ይገኛሉ። ጥራት ያለው የዘር ግንድ ከሰለሞንና ከሳባ የወረደው ሲሆን፥ ነገደ ዛጉዌ ግን ከሰለሞንም ቢፈልቅ ከሳባ ገረድ ነውና የሚወለደው ዝቅተኛነቱን ያምናሉ።

"…. ዛጉዌማ ከገረድ ነው የተወለደ
አያወጣው ወጥቶ ከዙፋን ወረደ…
የካም ልጆች ናችሁ እናንተ ጥቁሮች
ፈረንጆችም ናቸው የያፌት ልጆች" (ገጽ 12)

እርግጥ የሚያወጉለት ሻንቆ ጆሮ አልሰጣቸውም፥ ያቁዋርጣቸዋል።

"እንዲህ ያል ንግግር ያሰኛል አላቲ!
ባሻ አሸብር ከልካይ ልጠይቅህ እስቲ፥
ገና አንተ ነህና ኢትዮጵያዊ
አይደለሁም ልትል ጥቁር አፍሪቃዊ?" (ገጽ 13)

ቱሊ ሃበሻውን እንደ ከብት በመቁጠር እንዲህ ይላል፡-

"ስንመለከተው የኑሮአችሁ ቅጥ
ከንስሶች አኑዋኑዋር ምን ያህል ሲበልጥ
ጠቢብ ሰው በስራው መሬትን ሲቀድስ

ሁሉን በማሳመር ሲያጠዳና ሲያድስ
ደንቆሮ ህዝብ ግን እንደናንተ ያለ
በትልቅ ስንፍና የተንቀዋለለ
እንደ እንስሳ ሁሉ ምድርን አረከሳት ...” (ገጽ 38)

ይህ ወደሌላው የዘር ልዩነት መንስዔ ያሸጋግረናል፦ ወደ እውቀት ደረጃም፦

“ ህዝብ እየተራባ ዐለም ጎን ሲያንሳት
የመሬትዋም ስፋት በጣም ሲጣበብ
እንደኛ ያለው ህዝብ የሞላው ጥበብ
እንደናንተ ያለ የደከመውን
እንደ እንስሳ ሁሉ ፈጅቶ እያባረረ
ቤቱንም ሰውንም እየመነጠረ... ” (ገጽ 38)

ማስለቀቅ ይገባዋል። ከእውቀትም ጋራ የጦር ሃይልና የመሳሪያ ብልጫን ያካትትበታል። እንደ ባሻ አሸብር የሻንቆው ቀጥተኛ መልስ ሀበሻው ለቹሊው አይሰነዝርለትም። ነገር ግን ሃሳቡን በልቦናው አውጥቶ በማውረድ፥ እንደ አንስሳ የሚያስቆጥረው ጊዜያዊ ድክመት ወይም በታሪክ አጋጣሚ በዕውቀት ሁዋላ ቀርነት ሳይሆን ፋሽስታዊ ጭካኔና ኢሰብአዊነት መሆኑን ይገልጥለታል፦

“ትእቢት በልቡና እጅግ አሳድጎ
ሰውን አለማየት እንደራስ አድርጎ...
ያላንድ ርህራሄ እንደ ጭራቅ ሆደ
እረደው እረደው ማለትን መውደድ
አውሬስ የሚያሰኘው ይኸ ነው በውነቱ
ያለስም መሰየም ምን ያደርጋል ከንቱ !” (ገጽ 42)

“ዶሮን ሲያታልልዋት በመጫኛ ጣልዋት” እንዲሉ፥ የዘረኞችና የቅኝ ገዥዎች ዘዴ ለድርጊያቸው ክቡር ዓላማ መስጠት ነው። ስለዚህም ፋሽስቶች የመጣነው እናንተን ለማሰልጠን፥ ትምህርት ለማስፋፋት፥ አገር ለማልማት በሚል ሽፋን ነው።

የእሮሮው ቹሊ ግን እንዲህአይመጻደቅም ቀጥተኛ ነው። እናንተን እንደ እንስሳ ጠራርገን ባዶ መሬት ብቻ ነው እምንፈልገው ይላል። ለምን? መሬት ባለቤት የሌላት የሁሉ ነችና። ምን የሁሉ? የሃይለኛ ብቻ እንጅ፦

“ ሃይለኛ እየሄደ ያስገብራል የትም
መሬት የሁሉ ናት ባለቤት የላትም።” (ገጽ 38)

ሃይለኛው ይዞ፥ በገንዘቡ ሰርቶበት ከጥቅም ላይ ያውላታል እንጅ ለደካማውና ለደንቆሮው አይተውለትም ፦

“ ግን ደካማ ሲኖር የሌለው ጉልበት
የሚለቀው የለም የሚተኛለት።” (ገጽ 40)

ቹሊ የዘር የበላይነትን በደም ጥራት እነማርኮኒን በማጣቀስ ቢያሳብብም በጉልበት ጭምርም እንደሚገነባ ደግሞ አይክድም።......

ባሻ አሸብር፥ “የሞጃው ተወላጅ፥ የጠራሁት መንዚ ...” ቢሉም፥ በአገራቸው የጉልበትና የእውቀት አቅም ማነስ ምክንያት እንደተዋረዱም አልረሱትም።

“ ደረቲ ላይ ያለው ያገሬ ባንዲራ
ያምራል ተባለ እንጅ ከብሮም አልተፈራ።” (ገጽ 12)

በማለት ቁሳዊው የገንዘብና የጦር መሳሪያ እገዛ ለእኩልነት ማስፈለጉን ያምናሉ።

ቹሊው በኢትዮጵያ የጣሊያኖችን የበላይነት በደም ጥራትና በሃይል የሚገነባ መሆኑን በይፋ ቢገልጽም፥ የኢኮኖሚውን ፋይዳ በህቡዕነት ሳይዝ አልቀረም። ቁጭት መወጣትን፥ የአድዋን ቂም በቀልም አልዘለላትም።

“አድዋ ድል ብንሆን ሣ ዓመት ቆይተን
ይኸውና ዛሬ ተመልሰን መጥተን
.......
ደምን ለመበቀል ለመግዛትም በቃን።” (ገጽ 40)

የዘረኛነት መንስዔ አንዱ ህቡዕ የዝቅተኛነት ስሜትን ለመወጣት የሚወሰድ እርምጃ መሆኑ አያጠራጥርም። የነጭ ዘር በጥቁር ዘር ብዙ የሚቀናበት ነገር እንዳለው ይታወቃል። በቁመናው፥ በአካላዊ ብቃቱ፣ በመንፈሰ-ብሩህነቱና ከጭፍግ ልቡና ነጻነቱ ሁሉ ያስቀናዋል። የሰብዓዊ ስልጣኔ ቅድምናውም ያስቆጨዋል። የሚኖርበት መልክዓ-ምድር፥ የአየር ንብረቱም ምቀኝነት ሳያሳድርበት አልቀረም። ስለዚህም፥

‘‘ጥሩ አገር ይዛችሁ በከንቱ ስትኮሩ
ወይ አትሰሩበት ወይ ሰው አታሰሩ’’ (ገጽ 38)

በማለት የኢኮኖሚ ቅድሚያ ቀዳዳ ይሻል።

የዋሽንግቶኑ ነጭ በኢኮኖሚው ረገድ ፊት ለፊት ነው ባሻን የሚጋፈጣቸው።

‘‘ገበያ አላገኝም ደምበኞችም
እዚህ አንተን ካዩ ዳግመኛ አይመጡም
ስራ ስራ እኮ ነው አይገባህም እንዴ
ወግድ አትገተር ይቆዋረጣል ንግዴ!’’ (ገጽ 11)

‘‘ቢዝነስ ኢዝ ቢዝነስ’’ -- ነው ቁርጥ ያለው አቋሙ።

ስለግጥሞቹ ጭብጥ ይህን ያህል ከተመለከትን ወደስልታቸው ደግሞ እንዙር።

## 1.2 <u>የግጥሞቹ ስልቶች</u>

1.2.1 ሽ<u>ሙጥ :-</u> የዘመኑን እኪት ወይም እብደት በውስጠ-ዘያዊ ጽሁፍ ማጋለጥ የሽሙጥ ወይም፣አሽሙር ስልት ነው።<u>እሮሮም</u> ፥ <u>ባሻ አሸብርም</u> ውስጠ-ወይራዎች ናቸው። የኢትዮጵያው ቹሊ፣ የሀበሻን ድንቁርናና ዝቅተኛነት አጋንኖ ሲያንቋሽሽ ፥ የራሱን የባሰ ድክመት ወይም ጉድለት፣ በትዕቢታዊ ዘረኝነት ያንጸባርቃል። ለቋንቋዋውም ሆነ ለድርጊቱ ለከት የለውም። የስድቡን መዓት ሲያኾጎደጉደው ለሌላው ስሜት ምንም ፋይዳ አይሰጠውም። ይሁን እንጅ ነገሩ ሁሉ የማያወላዳቀጥተኛ ነው:- ከሀበሻ ጋር ጭራሽ ግንኙነት የማቋዋረጥን፣ በጋብቻም ሆነ በመኖሪያ ክልል – በጥብቅ ለያይቶ የማኖርን ስርዓት ይደነግጋል። የሀበሻውን የባህሪ ጉድለቶች ሲዘረዝርም:- በታላቅ ስንፍና ተንቀዋልሎ የሚኖር መሆኑን፥ ለዓለም የሚጠቅም አንድ ፋይዳ ያለው ስራ ያለመስራቱን፣ ነገር ግን በአጉል ኩራት የትውልድ ስፍራንና የአያት ቅድመ አያትን ርስትና ንብረት እያነሳ መንጠራወዙን፣ ከሁሉም በላይ ስለድንቁርናው መጠን ጭራሽ ግምት የሌለው መሆኑን ያሳውቀዋል። ስለዚህም ሀበሻው የተወራጅ ደረጃውን አውቆ ተሸቆጥቁጦ ማደር እንዳለበትና ቹሊው የበላይነቱን ለማረጋገጥ እጁን እንኩዋን በመጸየፍ ለሰላምታ እንደማይዘረጋለት ይገልጻል:-

‘‘ደግሞ ላበሻ ሰው ሰላምታ ስሰጥ
እጄን ዘርግቸለት እጁን መጨበጥ
ታላቅ ውርደት መስሎ ስለሚታየኝ
መቸም አላደርገው ለዚህ ኩሩ ነኝ... ’’ (ገጽ 39)

“ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ” ነው ምስጢሩ። አበሻው ለፈረንጁ ያለው ንቀት፥ ጽዩፍነት ከዚህ የላቀ መሆኑን ቿሊ እልተገነዘበም። ሆኖም ከፋሽስት አንደበት አንዳንድ ሀቆች በዘለፋ መልክም ቢሆን ለሀበሻው ድንጋይ ራስ ይወረወራሉ። ድንጋዩ መልዕክት ፈንክቶት ይገባው እንደሆን በማለት።

ነጮቹ በጥበብ ዓይነት ጌጥ በተሞሉ ከተሞች ሲኖሩ፥ ፋብሪካ በፋብሪካ፥ኢንዱስትሪ በኢንዱስትሪ ሲሆኑ፥ ሁብት ሲያከማቹና በስልክ፥ በኦቶሞቢል ሲመናሹ...

“ የሀበሻ ህዝብ ግን የሚሄደው ለብሶ

የቤት እቃው ሳይቀር ሁሉም የተውሶ!” (ገጽ 39)

እናም በዚህ ሁናቴ ከቀጠለ ለሀበሻው እጣ ፋንታው ዝርያውን ማጥፋትና ህልውናውን ከዚህ ዓለም መሰረዝ መሆኑን ቿሊ አጡዞ ሲደመድም፥ ለዚህ ጥፋት ሳቢያው የሀበሻው ድንቁርና ና ስንፍናው እንጅ ሌላ ተጠያቂ እንደማይኖር ያበስራል ፦

“እያመነመነ ከፉ ድንቁርና

ስለገደላችሁ የማይተው ስንፍና

ብልሃት አይገኝም ምንም ቢመረመር

እናንተን ጨርሶ ከማጥፋት በስተቀር!” (ገጽ 40)

ከበደ ሚካኤል ከአምሳ ዓመት በፊት ይኸንን ሲያስፍሩ፥ “ጆሮያለው ይስማ!” በማለት ነበር። የሰማቸው ቢኖር ...

ከሁለት አስርታት ያህል በሁዋላ የተከተላቸው ባለቅኔ መንግስቱ ለማ፥<u>በባሻ አሸብር በአሜሪካ</u> ያስፈረው አሽሙር ከዚህ ለየት ባለ አኩሁዋን ነበር።

ባሻ አሸብር፥ ኢትዮጵያ ከነበረው ቿሊ ስር በእሮሮ ከሚብከነከነው ሀበሻ ዓይነት የተለየ ግለሰብ ነበሩ። “የሞጃው ተወላጅ፥ የጠራሁት መንዜ! ...” እያሉ ካባቸውን ደርበውና ከዘራቸውን ይዘው የሚንጎማለሉ አበሻ ነበሩ፡ያውም በዋሽንግቶን፥ አሜሪካ! ታድያ አገጫቸውንና ጉንጫቸውን በቡጢ የሚያነጉል፥ ጥርሳቸውን የሚሸርፍ ዘረኛ አጋጠማቸዋ! እሳቸውም የዋዛ አይደሉም፤ በያዙት ከዘራ “ገርለጥ” አድርገውታል። ውጤታቸው ግን አላማረም፥ ነጩ በነጻ ሲለቀቅ እሳቸው በወህኒ ማቀቁ። ያውም ዲፕሎማት፤ የውጭ አገር መንግስት ሹም፥ ዘበጥያ ወረዱ - የውርደት ውርደት!

ውስጠ - ወይራው፥ ዘረኛነት በነጭ ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ በጥቁሩምዝንድ አለ ነው። ይሁን እንጅ ወህኒም ወርደው ይህ ሃቅ አልገባቸውም።

“የሞጃው ተወላጅ የጠራሁት መንዚ
ሸጎሌ ጊሚራ ተበዩ መያዚ
በግፍ እንደሆነ በውሸት ባሰት
አቃተኝ ማንንም ከቶ ማስረዳት!” (ገጽ 13)

እንኳዋን ሌላውን ሊያስረዱ ይቅርና፥ ራሳቸውም ያልተረዱትነገር ነበር። የተረዱት ነገር ቢኖር፥ የሳቸውን ልዩነት ነበር። ነጩም ጥቁሩም በእርግጥ አሉ። እነርሱም አዎ- እርስበርሳቸው ሲጋጩ የኖሩ ናቸው - እሳቸውን ግን ይኼ አይመለከታቸውም - አይነካካቸውም። ሀበሻ ናቸዋ - የሁሉም በላይ !

እዚያ ወሀኒ ላገኙት ሻንቆ፥ ይህን ልዩነታቸውን ወይም የበላይነታቸውን ሊያስረዱት ይሞክራሉ። እንደ ቺሊ በኢትዮጵያ፥ ዘር ይቆጥራሉ፤ ነገደ ሴማዊነታቸውን፥ ከሰለሞንና ንግስተ ሳባ ዝርያቸውን፥ ይዘረዝራሉ። የቆዳ ቀለማቸውንና የራስ ጸጉራቸውን ሳይቀር ለማስረጃ ያቀርባሉ፡-

“እንካ ጠጉሬን እየው!...
ፊቴን ተመልከተው
ቀይ ዳማ ነኝ እኔ -- ይሁን ጠይም ልባል
እኔን መቁጠሪያ ራስ የሚለኝ ሰው አብዶአል።” (ገጽ 12)

ውሃ ሊጠጡበት የገቡበትን ሆቴል ባለቤት ብቻ አይደለም በከዘራቸው የዠለጡት፥ ወሀኒ ያገኙትን አፍሮ - አሜሪካዊ ጭምር ነው በፍየል ምላሳቸው ጠቅ ያደረጉት። ይህም በጣም ያስገረመው ጥቁር አሜሪካዊ እንዲህ ይላል፡-

“ባሻ አሽብር ከልካይ ...
ገና አንተ ነህና ኢ - ት - ዮ - ጵ - ያ - ዊ
አይደለሁም ልትል ጥቁር አፍሪቃዊ!” (ገጽ 13)

አሁንም “ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ!” ነው ውስጠ - ወ ይራው።

የአሽሙሩ ልዩነት አንደኛው ማለትዩቹሊው በኢትዮጵያ ውረፋው በቀጥታ ሲሰነዘር፥ ያበሻው ባሜሪካ፡ በእጅ አዙር መነገሩ ነው። የቹሊውና ያበሻው ፍጥጫ ፊት ለፊት ነው። ጥቁር እና ነጭ። የባሻና የሻንቆ ፍጥጫ ጥቁር ለጥቁር ነው። በኢትዮጵያ፥ ጪቁዋኝና ተጨቁዋኝ፥ በአሜሪካ ፡ ሁለቱም የጭቆና ሰለባዎች።

የፉሽስቱ ውረፋ በኢትዮጵያዊው ዘንድ እሮሮ ቢፈጥርም በአንዳንድ ሀቁ ደግሞ

የምሬት ሳቅም ያስከትላል። የባሻ አሸብር ተመክሮ በአሳዛኝ ሳቢያ የመጣ ቢሆንም፣ ሁኔታው አስቂኝ ነው። ቹሊ ስቱፒድ ፋሽስት ነው፣ ባሻ አሸብር ግን ጮሌ ክሩክ -- ነገረኛ መንዜ። ባጠቃላይ ሲታይ፣ "ባሻ አሸብር" ጠቅላላ ድባቡ ፍግ ሲሆን፣ የተንተራሰበት ዳራ ግን እጅግ አሳዛኝና አስቂኝ ነው። የሁለቱም ባለቅኔዎች ስጋት የሰው ልጅ መሰልጠን ትርጉሙ ዘረኛነትን ወይም ትዕቢትን ማስከተሉ ነው።

"እኔስ በመጻህፍት ያየሁ ያነበብኩት" ይላሉ ከበደ ሚከኤል፦

ጥበብ ያደርገዋል የሰውን ልጅ ትሁት

እውቀት ርህራሄን ይሰጠዋል ለልብ

ሲባል ነበር እንጅ እንዲህ ያለ ስድብ

እንዴት ይናገራል የሰለጠነ ህዝብ ።" (ገጽ 43)

......

ዘረኛነት ከሰልጡን ህዝብ የማይጠበቅ ነው። በአፍ እኩልነትን እየለፈፉ በተግባር መቃረን የሰው ልጅ ሊያስታርቀው ያልቻለው ክስተት ሆኖ ኖሮአል።

በሁለቱ ስራዎች ላይ የሚታዩ የአጻጻፍ ስልቶችን በዝርዝር ለማየት ሳይሆን የዚህ ጽሁፍ አላማ፣ ጎልተው የሚታዩትን ለመንቀስና ለማውጣት ነው።

ከበደ ሚካኤልየወል ቤት ወይም መደበኛው ተብሎ በሚጠራውየአሰነኛኘት ዘየ ማይስትሮነት ተነግሮ ያለቀለት ስልት ነው። ይህ እንደ ውሃ የሚፈስ፣ወይም እንደ ሀር የሚለሰልስ አገጣጠም፣ ስራዎቻቸውን ፎርማሊስት ያደርጋቸዋል። ከፉኛ ስርዓት ጠባቂ ያስመስላቸዋል። ምናልባትም እንደ <u>እሮሮ</u> ግዙፍ ጭብጥ ለያዘ ድርሰት ይስማማ ይሆናል። ነገር ግን የደራሲውን ዘና ብሎ የሚገዋዝ አሳብ በስርዓቱደንቦች ውስጥ ይከፍፈውና ያጣብበዋል።

የመንግስቱ ለማ <u>ባሻ አሸብር</u> በመደበኛው ቤት አሰነኛኘት የተደረሰ ቢሆንም፣ አልፎ አልፎ ይዝናናል። የንግግራዊ ባህሪያትን የያዘ አካሄድም ይገኝበታል። ለአብነት ያህል፦

" እኔም ጎራ ያልሁት የሚጠጣ ነገር

ለመሻት መሆኑን --- ነግሬ --- ከወንበር --

ይቅርታዎን ጌታ! አዝናለሁ በጣሙ

ምናምኒት የለም በከንቱ አይድከሙ ..." (ገጽ 10)

የእለት ከእለታዊ አባባሎችን ማቀፉ፣ ስድ ንባባዊ ጣዕምን፣ እሙናዊነትንም ያላብሰዋል።

ሁለቱ ቅኔያት በጭብጥ አንድ ሆነው ሳለ ፣ የሚለያዩበት አቢይ ነጥብ ቢኖር፣ ጭብጡን በሚያስተላልፉበት ዘያቸው ነው። የከበደ ሚካኤል ቀጥታ አስተምህሮአዊ /ዳይዳክቲክ/ ነው። ይህንንም አይሸፍኑትም፦ ገና ከመግቢያው ላይ ፦

"የኢትዮጵያ ልጆች እናንት ወጣቶቹ

የአሁኑ ጊዜና የወደፊቶቹ .."

ብለው በመጀመር እንዲያጤኑት ያስገነዝባሉ። ስራቸውም:-

"ሰው ተገኘ ሲሆን ያለብትን እዳ

የሚያመለክት ነው ገልጦ የሚያስረዳ"

ብለው ሳይደብቁ ይገልጻሉ።

የመንግስቱ ለማ <u>ባሻ አሸብር</u> ግን ዓላማውን በይዘቱ ውስጥ አዋህዶ የሚጉዋዝ ነው። ተነጥሎ ወይም ታግሎ አይታይም። ባሻ አሸብር ታሪካቸውን እየዘከሩ እኔን ያየህ ተማር እንጅ፥ ይኸውልህ የማስተምርህ ትምህርት ብለው አይለፍፉም።

አንዱን ዘየ ከሌላው ለማበላለጥ አይደለም። ሁለቱምየሚያገለግሉበት ስፍራና ጊዜ አላቸው። "የጥበብነት መለዮ ጥበብነትን መደበቅ ነው" የሚለው መርሆ፥ ለትምህርት መስጭያ እንዲያገለግሉ የታቀዱ ስራዎችን አያካትትም።<u>እሮሮ</u> ሆን ተብሎ ለማስተማሪያ ሲቀርብ፥ በውን የደረሰ ታሪክን ለማስታወሻ የተደረሰ ስራ ነው። በዚህም ግቡን በትክክል መትቶአል። <u>ባሻ አሸብር</u> እያዝናና በህቡዕ ያለ ውነታን ወይም ክስተትን ፈልፍሎ በማውጣት በአንባቢው ዘንድ ግንዛቤውን ለማሳደር ሲባል የተደረሰ ነው። ስለሆነም ይህን ያህል ተገንዘብልኝ ብሎ አደራ አይልም። ግንዛቤውን ለተደራሲው ይተወዋል። በዚህም ያለጥርጥር ግቡን መትቶአል።

1.3 <u>መደምደሚያ</u> የሁለቱን ቅኔያትመደምደሚያዎች በመጨረሻ ላይ ማንሳት የባለ ቅኔዎቹን ርዕዮት ለመዳሰስ በመጠኑም ቢሆን ያስችላል። ከበደ ሚካኤል መለኮታዊ መፍትሄን ነው የሚጠሩት:-

"የሩሸስት መግት ቢበጅም ባይበጅ

ከሰው ጋር አይደለም ከእግዜር ጋር ነው እንጅ" ይላሉ።

(ገጽ 43)

ያው ሁሉን ነገር ያመጣው እግዚአብሄር ስለሆነ፥ እሱ እንዳመጣው እሱ ይፈታዋል ነው እምነታቸው። ጥብቅ እምነታቸው።

የመንግስቱ ለማ ዝነኛ መደምደሚያቃላት፥ "ስልቻ ቀልቀሎ፥ ቀልቀሎ ስልቻ፥ ...." እንደ መረዋ የሚያስተጋበት እውነት፥ ሰው ያው ሰው መሆኑን፥ መድህኑም ለራሱ እራሱ ብቻ መሆኑን ነው። ይህም ድምዳሜ በሁለቱ ጥቁሮች፥ በአበሻውና በአፍሮ - አሜሪካዊው መካከል ሲደረስበት፥ ተምሳሌነቱ ጥቁርን በጥቁር ማሻር እንደሚገባው ይጠቁማል። መፍትሄው ከራሳቸው አያልፍምና።

''ይመስገነው ገባኝ ከጊዜ በሁዋላ
አማሪ ጊሚራ ጋላና ሻንቅላ
ሱማሌ ኪኩዩ ሱዋሂሊ ባንቱ
ኩኑኑ ሉሉ ማሳይ ኔግሮ ባማንጉዋቱ
ማለት እንደሆነ ስልቻ ቀልቀሎ
ቀልቀሎ ስልቻ፤ ስልቻ ቀልቀሎ!'' (ገጽ 13)

ዋቢ መጻህፍት

ከበደ ሚካኤል ፥ 1960፡ ታሪክና ምሳሌ 3ኛ መጽሀፍ ፥ አዲስ አበባ ፡ ንግድ ማተሚያ ቤት።

መንግስቱ ለማ፥ 1967፡ ባሻ አሸብር በአሜሪካ ፥አዲስ አበባ ፡ ቸምበር ማተሚያ ቤት።